*ከፍ ያለ ተጽእኖ ለመፍጠር አነስተኛ ድጋፎች (SGSI)፡- ትብብር ለተሻለ ጾታዊ፣ የስነ-ተዋልዶ፣ የእናትነት፣ የጨቅላ ሕፃናት፣ የሕፃናት፣ እና የጉርምስና እድሜ ላይ ላሉ ልጆች ጤና*

**ለጾታዊ፣ የሥነ-ተዋልዶ፣ የእናቶች፣ የጨቅላ ሕፃን፣ የሕፃናት፣ እና በጉርምስና እድሜ ያሉ ልጆችን ጤና (SRMNCAH) ለማሻሻል የሚውሉ አነስተኛ ድጋፎችን ለመስጠት የጽንሰ-ሀሳብ ማመልከቻ ጥሪ**

***ዳራ፡-*** የCORE Group ተልእኮ በቂ አገልግሎት ላላገኙ ህዝቦች በተለይም ለሴቶች፣ ሕፃናት እና በጉርምስና እድሜ ላይ ላሉ ልጆች የማኅበረሰብ ጤና አጠባበቅ ተግባራትን በትብብር እና በመማር ማሻሻል እና ማስፋት ነው። በአካባቢ፣ በክልላዊ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሻሻለ አቅም የሚያመጣውን የእውቀት ልውውጥን የሚያበረታታ የትብብር እና ገለልተኛ ቦታን በመፍጠር፣ የዓለም አቀፍ የኅብረተሰብ ጤና ችግሮችን ለመፍታት የመሪነት ሚና የሚጫወቱ ብቁ ባለሙያዎችን አሰባስበናል።

የፆታዊ፣ የሥነ-ተዋልዶ፣ የእናቶች፣ የጨቅላ ሕፃናት፣ ሕፃናት እና በጉርምስና እድሜ ላይ ያሉ ልጆች ጤና (SRMNCAH) አገልግሎቶች, የአለም አቀፍ የጤና ሽፋን ግብን እና ዜጎች የተሟላ ጤንነት እና ደህንነትን እንዲያገኙ ስልታዊ የልማት ግብን ለማሳካት አስፈላጊ ናቸው። በዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት (LMICs) በተለይም በጉርምስና ዕድሜ የሚወልዱበት ዕድሜ ላይ ያሉ ሴቶች መካከል ከፍተኛ የሆነ ያልተሟላ ዘመናዊ የእርግዝና መከላከያ ፍላጎት እንዳለ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተጨማሪም ዝቅተኛ የገቢ መጠን ባለበት ሀገር ውስጥ የምትገኝ አንዷት ሴት በሕይወት ዘመኗ ከእናትነት ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የመሞት እድሏ ከፍተኛ ገቢ ባለበት ሀገር ውስጥ ከምትኖረው ሴት ጋር ሲነጻጸር በ130 እጥፍ ከፍ ያለ ነው። በአለም አቀፍ ደረጃ በ2018 ወደ 2.5 ሚሊዮን የሚጠጉ አዲስ የተወለዱ ሕፃናት የሞቱ ሲሆን፣ በአራስ ሕፃናት ላይ የሚከሰት ሞት ከአምስት ዓመት በታች ከሆኑ ሕፃናት ሞት 47 በመቶውን ይይዛል። ምንም እንኳን በሕፃናት በሕይወት መኖር ላይ መሻሻል ቢኖርም የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሕፃናት እና በጉርምስና እድሜ ያሉ ልጆች ሳይሟሉ የቀሩ የጤና ፍላጎቶች እንዲኖራቸው አድርጓል።

***የአነስተኛ ድጋፎች ዓላማ፡-*** CORE Group ብቁ ከሆኑ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች (NGOs) እና የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች (CSOs) ጋር በመተባበር በሁለት ቅድሚያ በሚሰጣቸው ሀገራት የ SRMNCAH አገልግሎቶችን እና ውጤቶችን ለማሻሻል ዋና ዋና መሰናክሎችን ለመፍታት አሳታፊ አላማ የያዙ አነስተኛ ድጋፎችን ይሰጣል፡- ***ሀገራቱም ኢትዮጵያ እና ኬንያ ናቸው።***

የአነስተኛ ድጋፎች የ SRMNCAH ፕሮግራምን፣ ፖሊሲን እና የፕሮግራም ትግበራን በሁለት ቅድሚያ በሚሰጣቸው ሀገራት ውስጥ ለማሻሻል የገንዘብ፣ የቴክኒክ እና ድርጅታዊ አቅምን ለመገንባት በሴቶች ለሚመሩ፣ በወጣቶች ለሚመሩ እና በአካል ጉዳተኞች ለሚመሩ አገር በቀል ድርጅቶች በማቅረብ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ይህ አካሄድ በሥርዓተ-ፆታ ሥር ነቀል ለውጥ ማምጣት፣ ጥራቱን የጠበቀ እንክብካቤ እና በጤና ፍትሃዊነት ላይ በማተኮር ለ SRMNCAH ተግዳሮቶች ማኅበረሰብ አቀፍ መፍትሄዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር የአካባቢ እና ብሄራዊ ድርጅቶችን የቴክኒክ እና ድርጅታዊ አቅም ያጠናክራል።

***የድጋፍ መጠን እና የድጋፍ ተቀባዮች የብቁነት መስፈርት፡-*** በዚህ ደረጃ፣ CORE Group በአጠቃላይ አምስት ድጋፎችን ለመስጠት በዝግጅት ላይ ነው፡-

1. በ18 -24 ወራት ውስጥ ተግባራዊ የሚደረጉ ለአምስት ዓመታት ወይም ከዚያ በላይ ሲሠሩ ለቆዩ ድርጅቶች እስከ $200,000 የሚደርሱ ሁለት ድጋፎች።

2. በ18-24 ወራት ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑ ከ1-5 ዓመታት ሲሠሩ ለቆዩ ድርጅቶች እያንዳንዳቸው እስከ $90,000 የሚደርሱ ሦስት ድጋፎች።

ድጋፎቹ የሚሰጡት ከሁለቱ ቅድሚያ ከሚሰጣቸው አገሮች ስኬታማ በሆነ መንገድ ብቁ ለሆኑ የNGOዎች ወይም CSOዎች አመልካቾች ነው።

***የብቃት መስፈርቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-***

1. በሀገሪቱ ውስጥ የተመዘገቡ፣ ይፋዊ፣ ወቅታዊ ምዝገባን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ NGOዎች ወይም CSOዎች።

2. በሴቶች፣ በወጣቶች ወይም በአካል ጉዳተኞች የሚመሩ NGOዎች ወይም CSOዎች፣

3. በ (የታቀደው) ጂኦግራፊያዊ የትግበራ ቦታዎች/ማኅበረሰብ ውስጥ ድርጅታቸው የሚገኝ NGOዎች ወይም CSOዎች፣

**የድጋፍ አሰጣጥ ደረጃዎች እና የጊዜ ገደብ፡-** ድጋፍ ለመቀበል የመጀመሪያው እርምጃ በ SRMNCAH ውስጥ የሚቀረፈውን ቁልፍ ተግዳሮት፣ የፕሮግራም ትግበራውን አላማ/ዎች፣ የፕሮግራም ትግበራ ዘዴ/አቀራረብ መግለጫ፣ የጂኦግራፊያዊ ቦታ፣ የጊዜ ገደብ (ከ18 እስከ 24 ወራት)፣ የትግበራ ዝግጅት እና የክትትልና የምዘና እቅዱን ጠቅለል አድርጎ የሚያቀርብ የተሳካ የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻ ማቅረብ ነው። ሁለተኛው እርምጃ የጽንሰ-ሀሳብ ማመልከቻው (ኮንሰፕት ኖት) ተቀባይነትን ሲያገኝ CORE Group ከተሳካላቸው የNGO/CSO አመልካቾች ጋር ዝርዝር እቅድ እና በጀት በማዘጋጀት ይሳተፋል። ዝርዝር የፕሮፖዛል እና የበጀት ዝግጅቱ ዝርዝር ነገሮች በኋላ ላይ ለስኬታማ የፅንሰ-ሀሳብ አመልካቾች ይጋራሉ።

ድጋፎቹን ለመስጠት እና ለመተግበር የሚጠበቀው የጊዜ ገደብ ማጠቃለያ እንደሚከተለው ነው፦

1. የፅንሰ-ሀሳብ ማስታወሻዎችን መገምገም እና መመዘን፦ 1 ወር።
2. NGOዎችን/CSOዎችን መምረጥ እና ከተመረጡት ጋር መነጋገር የአቅም ግምገማ እና የድጋፍ ዝግጁነት፦ 1 ወር።
3. በድርጅታዊ አቅም ማጠናከሪያ ዘዴዎች እና የቴክኒክ እቅድ ዝግጅት የበይነመረብ ትምህርታዊ ጉባኤዎች፣ ውይይቶች፣ ግብረ-መልሶች መሳተፍ እና አሳታፊ ሙሉ የእቅድ ዝግጅትን ማጠናቀቅ። 1 ወር
4. ድጋፍ መስጠት እና መተግበር፦ ከ 18 እስከ 24 ወራት።

**ድርጅታዊ አቅም ማጠናከር፡-** ከድጋፉ ዓላማዎች መካከል አንዱ የሀገር ውስጥ NGOዎች/CSOዎች አቅምን ማጠናከር ነው። CORE Group በተለያዩ አካባቢዎች ድርጅታዊ አቅማቸውን ለማጠናከር ድጋፍ ለሚያገኙ NGOዎች/CSOዎች በእያንዳንዱ NGO/CSO ልዩ ፍላጎቶች እና በድጋፉ አላማ መሰረት ነፃ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል። የአቅም ማጠናከሪያ ርእሶች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦

1. ድርጅታዊ ፖሊሲዎች እና መዋቅር።
2. ጥራት ያላቸው ፕሮፖዛሎችን ማዘጋጀት።
3. ፕሮግራሞች እንዴት እንደሚተገበሩ።
4. መረጃን መሰብሰብ እና መተንተን።
5. ውጤቶችን እንዴት መመዝገብ እና ውጤታማ ሪፖርቶችን መፃፍ እንደሚቻል።
6. አመራር እና አስተዳደር
7. የፋይናንስ ሥርዓቶች እና አስተዳደር
8. ክትትል እና ምዘና
9. ትስስር፣ እና አጋርነት
10. ድርጅታዊ የስጋት አስተዳደር ማዕቀፍ
11. የፕሮጀክት ዑደት አስተዳደር

**የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻ ርዕሶች፡-** የ SRMNCAH ፕሮግራሞች የተደራሽነት እጦትን፣ ጥራት የሌላቸው ወይም በዝቅተኛ ሁኔታ ጥቅም ላይ የሚውሉ ከፍተኛ ተጽእኖ ያላቸው የሕይወት አድን የፕሮግራም ትግበራዎችን የሚያስከትሉ ብዙ ተግዳሮቶች እና መሰናክሎች ያጋጥሟቸዋል። ሆኖም ግን፣ ሁሉም መሰናክሎች በመጠን እና በተጽዕኖቻቸው እኩል አይደሉም። የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻ ከፍተኛ ተፅእኖ ያላቸውን የፕሮግራም ትግበራዎች ተግባራዊ ማድረግ እንዳይቻል የሚያደርጉ ቁልፍ የሆኑትን መሰናክሎች መፍታት አለባቸው። እነዚህም የታለመው እና ከፍተኛ ውጤት ከሚኖራቸው የ SRMNCAH የፕሮግራም ትግበራዎች ተጠቃሚ እንዳይሆን እና ከፍተኛ ለሆነ

የእናቶች፣ ለጨቅላ ሕፃናት እና ለሕፃናት ሞት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ እንቅፋቶች ናቸው። ስለዚህ፣ የተገደቡት ድጋፎች የሚኖራቸውን

1. በገጠር አካባቢዎች ላሉ ሴቶች ያልተሟላ ዘመናዊ የወሊድ መከላከያ ፍላጎት።
2. በጉርምስና ዕድሜ ላይ ያሉ ሴት ልጆች ያለ ዕድሜ ጋብቻ/እርግዝና።
3. በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች ላይ ያተኮረ የቤተሰብ ዕቅድ የፕሮግራም ትግበራዎችበገጠር አካባቢዎች ላሉ ሴቶች እና ጨቅላ ሕፃናት የድንገተኛ ጊዜ የወሊድ ህክምና እና የጨቅላ ሕፃናት እንክብካቤ ተደራሽነት።
4. በቤት ውስጥ መውለድ፣ በተለይም በኢትዮጵያ በገጠሩማህበረሰቦች ውስጥ ላሉ ሴቶች ብቻ።
5. የእናቶች፣ የጨቅላ ሕፃናት እና የሕፃናት አመጋገብ
6. በማህበረሰብ ደረጃ ውጤታማ ያልሆነ በልጅነት የሚከሰት ትኩሳት ቁጥጥር።
7. ምንም ዓይነት ክትባት ወስደው የማያውቁ ሕፃናትን ጨምሮ ከአምስት አመት በታች ለሆኑ ሕፃናት ክትባትን መጨመር
8. ለስደተኞች ወይም ለአገር ውስጥ ተፈናቃዮች ያልተሟሉ የእናቶች እና የሕፃናት የጤና ፍላጎቶች።
9. ያልተሟላ የልዩ ቡድኖች ጾታዊ እና የሥነ-ተዋልዶ ጤና ፍላጎቶች ለምሳሌ፤ አካል ጉዳተኛ ሴቶች፣ (ሌዝቢያን፣ ጌይ፣ ትራንስጀንደር፣ ባይሴክሹዋል እና ክዊር) LGTBQ ማኅበረሰብ እና ሌሎች ልዩ ቡድኖች።
10. ለ SRMNCAH ሌሎች ቁልፍ መሰናክሎች። የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻዎች ሌላኛው እንቅፋት ምን እንደሆነ በበቂ ሁኔታ መግለጽ አለባቸው።

ተጽእኖ ከፍ ለማድረግ፣ የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻዎች ከሚከተሉት ቁልፍ መሰናክሎች ውስጥ አንዱን መፍታት አለባቸው፡-

***እባክዎን ያስተውሉ፡- ተሚጋችነት ተለይቶ የተወሰነ የፕሮግራም ትግበራ ቦታ አይደለም፤ በግምገማው ወቅት ወጥነት እንዲኖር ሁሉም የጽንሰ-ሀሳብ ማመልከቻዎች መግባት ያለባቸው በእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው።***

**የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻዎች ማቅረቢያ መመሪያዎች፡-** የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻ **ከሰባት ገጾች** በላይ መሆን የለበትም። የሚከተሉትን ርእሶች ጨምሮ በአጭር እና ግልጽ ቋንቋ በእንግሊዝኛ መፃፍ አለበት፡-

**1. የአመልካቹን NGO/CSO አጭር መግለጫ ያካትቱ፡-** የአመልካቹን NGO/CSO ስም፣ አድራሻ፣ የመገኛ መረጃ፣ ዋና ተጠሪ ስም፣ የእሷ/የእሱ ኢሜይል አድራሻ እና ስልክ ቁጥር፣ ድርጅቱ የተመዘገበበት ቀን፣ የድርጅቱ አቅም አጭር መግለጫ (የሠራተኛ አደረጃጀት፣ መዋቅር፣ የሥራዎች መጠን፣ የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት የሚገኝበት ቦታ፣ የድርጅቱ ቅርንጫፍ ቢሮዎች ቁጥር እና ስርጭት፣ በአጠቃላይ እና በ RMNCAH ድጋፎች ላይ ልምድ ካለ፣ ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ተመሳሳይነት ያለው የገንዘብ ድጋፍ አስተዳደር እና በሌሎች አገሮች ውስጥ መገኘት እና ልምድ ካለ። (1 ገጽ ቢሆን ይመከራል)።

**2. ለየትኛው የድጋፍ መጠን እንደሚያመለክቱ ይግለጹ፡-** ትልቁ ድጋፍ (እስከ $200,000)፣ ወይም ትንሹ ድጋፍ (እስከ $90,000) ሊሆን ይችላል።

**3. የተመረጠውን የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻ ርዕስ እና የተመረጠበትን ምክንያት ይግለጹ፡-** በድጋፉ የሚቀረፈውን ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸው የ SRMNCAH ፕሮግራም ትግበራዎች (ከላይ ካለው ዝርዝር) እንዳይተገበሩ የሚያደናቅፈውን ቁልፍ እንቅፋት ይምረጡ። ይህንን እንቅፋት የመረጡበትን ምክንያት ከሀገርዎ እና ከአካባቢው ሁኔታ አንጻር ያብራሩ እና በሀገርዎ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ማስረጃዎችን/ምሳሌዎችን ያቅርቡ። በሚቻልበት ጊዜ የተመረጠውን እንቅፋት ምርጫ ምክንያት ያቅርቡ። (½ ገጽ ቢሆን ይመከራል) የተመረጠው እንቅፋት በ"ሌሎች ቁልፍ እንቅፋቶች" ምድብ ስር ከሆነ፣ እባክዎትን እንቅፋቱ ለምን

በሀገርዎ እና በአካባቢዎ ውስጥ ቁልፍ እንደሆነ ያብራሩ።

**4. የተመረጠውን እንቅፋት ለመፍታት የፕሮግራም ትግበራውን ይግለጹ፡-** ይህ የማህበረሰብ አቀፍ የፕሮግራም ትግበራ/የመፍትሄውን ልዩ ዓላማ/ዎች፣ የሚጠበቁ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ውጤቶች (ውጤቶች) እና በድጋፉ ቆይታ ውስጥ የሚከናወኑ ልዩ ተግባራት፣ የፕሮግራም ትግበራውን ለማስፈጸም አቀራረብ/ዘዴ፣ የፕሮግራም ትግበራው ጂኦግራፊያዊ ቦታ እና ከዋናው መሥሪያ ቤት/ነባር ፕሮግራሞች ጋር የሚኖረው ውህደት፣ ለአፈፃፀሙ ኃላፊነት የሚወስዱ ሠራተኞች፣ ድጋፉን ለመተግበር አስተዳደራዊ እና የገንዘብ/ሪፖርት አደራረግ ዝግጅቶች፣ ጥራት ያለው የቴክኒክ እና የፋይናንስ ሪፖርቶች ለማዘጋጀት የ NGO/CSO አቅም፣ በአፈፃፀሙ ላይ የሚሳተፉ የሀገር ውስጥ ባለድርሻ አካላት እና የፕሮግራም ትግበራ ጊዜን ጨምሮ ግልፅ የስራ እቅድን ሊያካትት ይገባል። (2 ገጽ ቢሆን ይመከራል)

**5. የክትትልና ምዘና ዕቅዱን ይግለጹ፡-** የድጋፉን ዓላማ/ዎች ለማሳካት የሚጠበቁትን የፕሮግራም ትግበራ ውጤቶች ለመከታተል የሚለኩ ዋና ዋና አመልካቾችን፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን እና መሳሪያዎችን፣ እንዲሁም የመረጃ ትንተና እና የአጠቃቀም ዘዴዎችን ከማረጋገጫ ዘዴዎች ጋር ያካትቱ። የሥርዓተ-ፆታ መርሆችን/ጠቋሚዎችን እንዴት እንደሚያካትቱ ያብራሩ። (1 ገጽ ቢሆን ይመከራል)።

**6. የፕሮግራም ትግበራን ልምድ እና ውጤት በስፋት ለመተግበር የሚቻልበትን ሁኔታ እና ዕቅድን ይግለጹ፡-** የድጋፉ ውጤቶች ለሰፊ የፖሊሲ ለውጥ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ አሠራር ማሻሻያ ወይም ውጤታማ የማኅበረሰብ ተሳትፎ አቀራረቦችን ለመደገፍ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። ይህ ክፍል በአገር አቀፍና በክፍለ-ሀገር ደረጃ የተገኘውን ልምድና የድጋፉን ውጤቶች ተጠቅመው የተመረጠውን ተግዳሮት በመቅረፍ ሰፊ መሻሻል ለማምጣት የታቀዱ ዋና ዋና ባለድርሻ አካላትን ዝርዝር ማካተት አለበት። የድጋፉን ውጤት ለሰፊ ትግበራ እንዲያጸድቁ የዋና ዋና ባለድርሻ አካላትን ፈቃድ ለማግኘት ከእነዚህ አካላት ጋር ለመስራት የሚተገበረውን አካሄድ አጭር መግለጫ ያካትቱ። (1 ገጽ ቢሆን ይመከራል)።

**7. ድርጅታዊ አቅምዎን የማጠናከር አስፈላጊነቶችን ይግለጹ፡-** የድርጅትዎን አቅም ማለትም ጥንካሬዎች ዳራ እና አንዳንድ ዝርዝሮችን እንዲሁም ሊሻሻሉ የሚገባቸውን ዘርፎች (ክፍተቶች) ይግለጹ። ይህ ክፍል በግልጽ በማስረጃ የተደገፉና ቅድሚያ የሚሰጣቸው የአደረጃጀት የአቅም ክፍተቶችን፣ የድርጅቱን ክፍተቶች መፍትሄ ካገኙ በኋላ የሚጠበቀውን ሁኔታ፣ የፕሮግራም ትግበራውን ተግባራዊ ለማድረግ አሳታፊ አካሄድ፣ በዚህ ላይ ያለ ድርጅታዊ ቁርጠኝነት እና በኢትዮጵያ እና በኬንያ ከሚገኙ አቻ NGOዎች እና CSOዎች ጋር እውቀትን ለመካፈል ፈቃደኛ መሆንን በግልፅ ማቅረብ ይኖርበታል። ከላይ"የድርጅታዊ አቅም ማጠናከሪያ" ስር ከተዘረዘሩት ድርጅታዊ የአቅም ማጎልበቻ ምሳሌ ውስጥ ይምረጡ ወይም ከድርጅትዎ ልዩ ፍላጎቶች ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ሌሎች ድርጅታዊ አምዶች/አካላትን ያካትቱ። (1 ገጽ ቢሆን ይመከራል)።

**8. በጀት፡-** የተቀመጡትን አላማዎች ለማሳካት ለታቀዱት ተግባራት በግልፅ በጀት መመደብ አለበት። በፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻው የተመለከቱት የበጀት መጠኖች በገበያው ተቀባይነት ያለው እንዲሁም ምክንያታዊ የሆነ ዝርዝር እና ትክክለኛ ግምት የሚያንፀባርቅ እና የታቀዱ ተግባራትን የሚያሳይ መሆን አለበት።

**በፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻዎች ዝግጅት ላይ የሚያስፈልጉ መረጃዎች፡-** ፍላጎት ያላቸው NGOዎች/CSOዎች ስለ አነስተኛ ድጋፎች ፕሮጀክት ዓላማ እና አቀራረብ ማብራሪያ ለመስጠት በሚዘጋጀው የበይነ መረብ መድረክ ላይ የሚሰጡ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት መመዝገብ ይችላሉ።

ክፍለ-ጊዜው ሰኔ 3 2017 (June 10, 2025) ከቀኑ 8:30 (2:30PM EAT) ላይ ይካሄዳል። ለክፍለ-ጊዜው ለመመዝገብ **እዚህ** ን ይጫኑ።

**የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻዎች ምዘና መሥፈርት፡-**

CORE Group ሁሉንም የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻዎች በምዘና ኮሚቴ በኩል የሚከተሉትን በሚያካትት እና ቀድሞ በወጣ መሥፈርት መሠረት የሚመዝን ይሆናል፡-

1. የአመልካች ድርጅት የብቃት ሁኔታ፡- ብቁ ከሆኑ NGOዎች/CSOዎች የቀረቡ የፅንሰ-ሐሳብ ማመልከቻዎች ብቻ ከግምት ውስጥ ይገባሉ (ከላይ ያሉ የብቁነት መሥፈርቶን ይመልከቱ)። ከፍተኛ ጥራት ያለው የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻ የሚያቀርቡ NGOዎች/CSOዎች ከመንግሥት የምዝገባ ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ።

2. የአመልካች NGO/CSO አቅም፡- CORE Group ውስን አቅም ያላቸው አነስተኛ ድርጅቶች እንዲያመለክቱ ያበረታታል። ይሁን እንጂ የድጋፍ አተገባበሩን ስኬታማ ለማድረግ አመልካቹ ድርጅት ድጋፉን ተግባራዊ ለማድረግ መሰረታዊ የሰው ኃይል፣ የፋይናንስ ሥርዓት እና አስተዳደራዊ አቅም ሊኖረው ይገባል። ይህ የሰራተኞችን ቴክኒካዊ አቅም ይጨምራል፣

3. አስተዳደራዊ እና ፋይናንስ አስተዳደርን እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ሥርዓት፣ NGO/CSO በድጋፍ አተገባበር ቦታ ላይ የመገኘት መጠን እና በአካባቢያዊ እና በሀገራዊ ደረጃ ቁልፍ ከሆኑ ውሳኔ ሰጪዎች ጋር ድርጅቱ ያለውን ግንኙነትን ማካተት አለበት።

4. የታቀደው ፕሮግራም ትግበራ ግልጽነት፡- የተገለጸውን ዓላማ/ዎች ግልጽነት (የተለየ፣ ሊለካ የሚችል፣ ተጨባጭ፣ ከተወሰነ የጊዜ ገደብ ጋር) ጨምሮ ማቅረብ። ከላይ ባሉት መመሪያዎች ውስጥ እንደተገለጸው የአተገባበር ዘዴ/አቀራረብ ግልጽነት እና ተአማኒነት ያስፈልጋል።

5. የሥራ እቅድ እና የክትትልና ምዘና እቅድ ግልጽነት እና ተአማኒነት፡- ከላይ ባሉት መመሪያዎች መሠረት።

6. የፕሮግራም ትግበራውን ልምድ እና ውጤቶችን በሰፊው ለመጠቀም የአጠቃላይ ድጋፉ ግልፅነት እና ተአማኒነት፡- ከላይ ባሉት መመሪያዎች መሠረት።

**የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻ የማስገቢያ የመጨረሻ ቀን እና የኢሜይል አድራሻ፡-**

ብቁ አመልካቾች የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻቸውን እስከ ሰኔ 18 2017 (June 25, 2025) ቀን ድረስ ማስገባት አለባቸው፡- ጁን 16፣ 2025

የፅንሰ-ሀሳብ ማመልከቻዎች ወደሚከተለው በኢሜይል አባሪ መላክ አለባቸው፡- Grants@Coregroup.org

የኢሜይሉ ርዕሰ-ጉዳይ "የፅንሰ-ሀሳብ ማቅረቢያ ማመልከቻ SGSI - የአመልካች NGO/CSO ስም/ ሀገር" መሆን አለበት ("Concept Note Application on SGSI – name of NGO/CSO/Country of Applicant)

ኢሜይሉ የተጠሪውን ስም፣ የእሷ/የእሱ ኢሜይል አድራሻ እና የሞባይል ቁጥርን ማካተት አለበት።